
# የካፒታል ገበያ መሰረተ ልማቶችን በቴክኖሎጂ መደገፍ ገበያ ስርዓት ውስጥ ያላቸው አስተዋፅኦ



## መግቢያ

የካፒታል ገበያ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ የደም ስር ነው። ይህ ገበያ ኢንቨስተሮች የሚተማመኑበት፣ ውጤታማ እና ፋይዳ ያለው ገበያ የሚሆነው ጠንካራ የገበያ እና የግብይት መሰረተ ልማት ሲኖር መሆኑን ልብ ይሏል። ብዙውን ጊዜ ስለካፒታል ገበያ ሲነሳ ትኩረቱ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት እና የዋጋ መዋዠቅ ላይ ብቻ ይሆናል።

ነገር ግን ከእነዚህ ክንውኖች በስተጀርባ ገበያው ታዓማኒነት እንዲኖረው ደጋግፎ የያዘው የቴክኖሎጂ፣ የህግ እና የተቋማት ስብስብ መሰረተ ልማት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ ጽሁፍ የካፒታል ገበያ መሰረተ ልማት ውስጥ ዋና ዋና አካላት የሆኑትን ክፍያ፣ ርክክብ እና ቴክኖሎጂን እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1248/2013 የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በጥልቀት እንዳስሳለን።

የካፒታል ገበያዎች የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተሮች ሲሆኑ ቁጠባን ወደ ውጤታማ ኢንቨስትመንቶች የሚቀይሩ ናቸው። ጠንካራ፣ እምነት የሚጣልበት እና ቀልጣፋ የፋይናንስ ስርዓት እውነተኛ መሠረት የሚገኘው ውስብስብ፣ ብዙ ጊዜ የማይታዩ የክፍያ እና የርክክብ ሂደቶች ውስጥ ነው። እነዚህ ዘዴዎች አንድ ግብይት አንዴ ከተፈጸመ በኋላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና የገንዘብ ዝውውር ደህንነቱ በተጠበቀ እና በማይሻር ሁኔታ መጠናቀቁን ያረጋግጣሉ።

የካፒታል ገበያ አዋጅ የቁጥጥር ማዕቀፍን በመዘርጋት አደጋን የሚቀንስ፣ ኢንቨስተሮችን የሚጠብቅ እና ስልታዊ የመቋቋም አቅምን የሚያረጋግጥ፣ የካፒታል ገበያ ተቋማትን ደንቦችን እና የቴክኖሎጂ ደረጃዎችን የሚወስን ነው። ይህ ጽሑፍ የክፍያ እና ርክክብ ወሳኝ ክፍሎችን ከካፒታል ገበያ አዋጅ አንጻር ይተነትናል፣

# የካፒታል ገበያ መሰረተ ልማቶችን በቴክኖሎጂ መደገፍ ገበያ ስርዓት ውስጥ ያላቸው አስተዋፅኦ

## የካፒታል ገበያ መሰረተ ልማት

የካፒታል ገበያ መሰረተ ልማት ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው የሚከናወንበት ስርአት ነው። ይህ ሥርዓት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የግብይት ሥርዓትን፣ የማዕከላዊ ሰነደሙዓ ለንዋይ ማከማቻ ግምጃ ቤትን እና የክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ ተቋማትን ያካትታል።
ኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን የመሰረተችው ለሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛው፣ የመንግስትን የፋይናንስ ጫና ለመቀነስና መንግስት ለልማት የሚፈልገውን ገንዘብ ከባንክ ብድር ይልቅ በቦንድ ሽያጭ እንዲያገኝ ለማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የግል ዘርፉን ለማበረታታትና የረጅም ጊዜ ካፒታል ምንጮችን ለማፍራት ነው። ።ይህ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን መሰረተ ልማቱ ታማኝና የኢንቨስተሮችን መብት በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ፋይዳ ሊኖረው ይገባልየካፒታል ገበያ አዋጅ 1248/2013 አንቀጽ 44 ስለ ክፍያእና ርክክብ በግልጽ የደነገገ ሲሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ አገልግሎት የሚሰጡ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ግዴታዎችን የሚፈጽሙት ለእያንዳንዱ ርክክብ ክፍያዎችን በመፈጸም መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል።

## ክፍያ እና ርክክብ

የካፒታል ገበያ መሠረተ ልማትን አስፈላጊነት ለመረዳት፣ ሁለቱን ዋና ዋና ደረጃዎች መረዳት ግድ ይላል። ክፍያ ማጣራት እና መፈጸም በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተከናወኑ ግብይቶችን የማስታረቅ እና የማረጋገጥ ሂደት ሲሆን ርክክብ ደግሞ ግብይቱን ለማጠናቀቅ የገንዘብ እና የሰነዶቹን ባለቤትነት ዝውውር የማድረግ ሂደት ነው። የክፍያ ማጣራቱ ሂደት “ማን ምን ዕዳ እንዳለበት” የሚወስን ሲሆን ርክክቡ ደግሞ እነዚያን ግዴታዎች የሚፈጸሙበት እና የሚሟሉበት ደረጃ ነው። የክፍያ ማጣራት ከግብይት በኃላ የሚከናወን ሂደት ሲሆን የገዢና የሻጭ ግዴታዎች የሚረጋገጡበት፣ ማን ምን መክፈል እንዳለብት የሚወሰንበት እና ግብይቱ ትክክል መሆኑን በመመርመር ልክ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ክፍያ ማጣራት ማለት በገበያ ላይ የተፈጸመ ግብይት ከተገቢነት አንጻር መፈተሸ፣ ማን ምን ያህል መክፈል እንዳለበትና ማን ምን ያህል ሰነድ እንደሚቀበል የማስላት ሂደት ነው። ይህን አገልግሎት የሚሰጡት በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ናቸው። ይህን አገልግሎት የሚሰጡት ተቋማት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ የስጋት አስተዳደር አንዱ ነው። ለምሳሌ አንድ ኢንቨስተር አክሲዮን ገዝቶ ገንዘቡን ባይከፍል ወይም አንድ ሻጭ አክሲዮኑን ባያስረክብ ገበያው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። የክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚአገልግሎት የሚሰጡት ተቋማት ይህ ስጋት እንዳይከሰት ዋስትና በመሆን ግብይቱ በሰላም እንዲጠናቀቅ ያደርጋሉ። እነዚህ የክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ አገልግሎት ሰጪዎች በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ጥብቅ ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው በአዋጁ መሰረት የክፍያ አለመፈጸም (Default) ቢከሰት እንኳ ገበያው እንዳይወድቅ የሚያደርጉ የመከላከያ ዘዴዎች (Default Management system) እንዲኖራቸው ይገደዳሉ።

# የቴክኖሎጂ አስፈላጊነት እና የዲጂታል ምዝገባ

ዘመናዊ የካፒታል ገበያ ያለ ቴክኖሎጂ ሊታሰብ አይችልም። በወረቀት ላይ የተመሰረተ የሰነድ ሙአለ ንዋይ ግብይት ስጋቶች የበዙበት ከመሆኑም በላይ ፈጣን ግብይትን አያረጋግጥም። ቴክኖሎጂ በካፒታል ገበያ ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ሚናዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ፡

ተዓማኒነት ማሳደግ፡- የቴክኖሎጂ መዝገቦች ግልጽና የማይለወጡ በመሆናቸው ማጭበርበርን ይቀንሳሉ፣

ተደራሽነት፡-ማንኛውም ኢንቨስተር ከያለበት ቦታ ሆኖ በሞባይል ስልኩ አማካኝነት ግብይት እንዲፈጽም ያስችላሉ፣

ፍጥነት፡- ግብይቶች በሰከንዶች ውስጥ ተፈጽመው ክፍያ ማጣራት እና ርክክቡ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያደርጋሉ፣

የመረጃ ደህንነት፡- የኢንቨስተሮችን የግልመረጃና የሀብት መጠን በከፍተኛ ሚስጥራዊነት ይጠብቃሉ፣

ማዕከላዊ ግምጃ ቤቱ የክፍያ እና ርክክብ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም ከገበያው የሚተላለፉለትን ግብይቶች በማጣራት ማለትም ሻጭ የሸጠው ሰነድ ያለውን መጠን መሆኑን፣ ገዥም ያለው ገንዘብ ሰነዱን ለመግዛት በቂ መሆኑን የማጣራት ሥራ ያከናውናል።ኢንቨስተሮች ሰነዳቸው እና ገንዘባቸው በአስተማማኝ ሁኔታ መያዙንና ንብረታቸው በዲጂታል መዝገብ መስፈሩን ሲያውቁ በገበያው ውስጥ በንቃት መሳተፍ ይጀምራሉ።

---

# የህግ ከለላ እና የአዋጁ ጥብቅ ድንጋጌዎች

የካፒታል ገበያ አዋጅ ለእነዚህ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች ህጋዊ መሰረት ጥሏል።
ቁልፍ ተቋማትን ያቋቁማል እና ይቆጣጠራል፡- አዋጁ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን፣ ማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገንን እና ማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤትን ለማቋቋም ህጋዊ መሰረት ጥሏል። አዋጁ የእነዚህን ተቋማት ሚናቸውን፣ ኃላፊነቶቻቸውን እና የአስተዳደር አወቃቀሮቻቸውን በተወሰነ መልኩ የሚያሳይ ሲሆን ይህን ለማስፈጸም የወጣው ለሕዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋችን ግዑዝ አልባ ማድረግ መመሪያ ቁ.1047/2017 ስለ እያንዳንዱ ተቋማት አሰራር እና ቁጥጥር ይደነግጋል። ህጋዊ እርግጠኝነት፡- አዋጁ በማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን ለሰነድ ሻጭ እና ገዥ ሁለቱም ወገኖች የሚሰጡ ዋስትናዎችን እንዲሁም በግምጃ ቤቱ በኩል ደግሞ ሰነዶችን ግዑዝ አልባ አድርጎ የመያዝ፣

ግብይት ሲፈጸምባቸው ክፍያን ማጣራት፣ የርክክብ እና የማስተላለፍ አሰራርን ይደነግጋል ። በተጨማሪ አዋጁ በምስክር ወረቀት አይነት የሚገኙ የካፒታል ገበያ የደርሻ ወይም የብድር ሰነዶች በግምጃ ቤቱ በግዑዝ አልባ አይነት በመተካት ህጋዊ ባለቤትነትን እንደሚያረጋግጥ ያመላክታል።
የአደጋ አስተዳደር ማዕቀፎች አስገዳጅነት፡ አዋጁ ለካፒታል ገበያ ባለሥልጣን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን፣ ማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገንን እና ማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤትን ዝቅተኛ የካፒታል መመዘኛን፣ የህዳግ አሰባሰብን እና በማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን በኩል ያልተከፈሉ እዳዎችን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓቶች በተመለከተ መመሪዎችን እንዲያወጣ ስልጣን ይሰጣል።
ቅልጥፍናን እና ግልጽነትን ያበረታታል፡ ከግብይት በኋላ የሚደረጉ የክፍያ ማጣራት እና ርክክብ ሁደቶች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በፍጥነት የሚፈጸሙ በመሆናቸው የግብይት ሂደቱ የፈጣን እና ቀልጣፋ ይሆናል። በካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 50 የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና

ክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ አገልግሎት ሰጪዎች የተወሰኑሁኔታዎችሲከሰቱወዲያውኑለባለስል ጣኑማሳወቅእንዳለባቸው ተደንግጎ ይገኛል። ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የመጀመሪያው ባለሥልጣኑ እንዲያሳውቅ የሚጠበቅበት፡ ተቃራኒ ወገን ግዴታ ፈጻሚው በርክክብና ክፍያ ወቅት ውስጠ-ደንቦች አለማክበሩን የደረሰበት እንደሆነ፣ በመቀጠልም ተቃራኒ ወገን ግዴታ ፈጻሚ የገንዘብ አቋም የመዋዠቅ ምልክት እያሳየ መምጣቱ ወይም የማያስተማን መሆኑ ሲገምት ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ግዴታ አለበት።
ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ ልዩ ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን በተለይ አንድ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ አገልግሎት ሰጪ አባል ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ አባል ቢከስር ወይም የፍርድ ቤት እገዳ ቢኖርበት እንኳን በካፒታል ገበያው ውስጥ የተጀመረ የርክክብ እና ክፍያ ሂደት ሊደናቀፍ አይችልም። ይህ ማለት የገበያው ደህንነት ከግለሰቦች ወይም ከኩባንያዎች መክሰር በላይ ቅድሚያ ይሰጠዋል ማለት ነው።

# አስተዳደራዊ እርምጃዎች

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ በፍቃዱ ላይ ከተመለከተው ውጪ ሌላ ሥራ ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤ ከባለስልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ ላይ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ጥሶ ከተገኝ፣ በባለሥልጣኑ የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ጥሶ ከተገኘ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠ እና ሌሎች መሰል ጥፋቶችን ፈጽሞ ከተገኝ፣ ባለስልጣኑ ጉዳዩን መርምሮ ከገንዘብ መቀጮ፣ እገዳ እስከ ፈቃድ መሰረዝ ሊያደርስ የሚችል ቅጣት መጣል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ አገልግሎት ሰጪው ወይም አስቀማጩ በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅሬታ ከተሰማው ጉዳዩን ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ እንዲታይለት ማድረግ ይችላል፡፡